በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

የአስሎ ቅዱስ ገብርኤልና አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦ/ተ ቤተ-ክርስቲያን ከዚህ ባታች የተጠቀሱትን ሰባት ክፍሎች አቋቁሞና አቅፎ ይንቀሣቀሣል። እያንዳንዱ ክፍል ያከነወነውን ዝርዝር ሪፖርት ለሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔው ያቀረበ ሲሆን ሁሉንም ለማቅረብ ጊዜ የማይበቃው ስለሆነ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔው አንኳር አንኳር የሆነውን ብቻ ጨምቆና አሳጥሮ ለማቅረብ ሞክሯል። ከጠቀሡት የአገልግሎት ዋና ከፍሎችና ንዑሳን ክፍሎች መካከል በሰ/መ/አ/ጉባዔው አቀራረብ በበቂ ሁኔታ ያልተገለጠ ክንውን አለ ብሎ የሚያስብ የአገልግሎት ክፍል መታለፍ የለበትም የሚለውን አንኳር ነጥብ በሊቀ መንበሩ በኩል በአጭሩ መጨመር ይችላል።

በመቀጠል ምእመናን ለሚፈልጉት አገልግሎት፣ አስተዋጽዖና ማንቸውም መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር መገናኘት እንዲችሉ የአግልግሎት ከፍሎችን፣ ንዑሳን ክፍሎችንና ሥራ አስፈጻሚዎቻቸውን በማሳወቅ እንጀምራለን።
ከዚያም ከጃኗሪ 01, 2016 እስከ ጁን 30/2016 በ6 ወር ውስጥ በቤተ-ክርስቲያናችን የተከናወኑ ዋና ዋና ክንውኖችን በማሳጠር አቀርባለሁ።

# የአገልግሎት ክፍሎችና ሥራ አስፈጻሚዎች

## 1/ የኦዲትና ኢንስፔክሺን ኮሚቴ

| ስም ዝርዝር | | | ሥራ | ስልክ |
|---|---|---|---|---|
| አቶ | ደባሱ | መሰሉ | ኦዲተር | 48190269/99543515 |
| » | ሺፈራው | ዘለቀ | ኢንስፐክተር | 90727322 |

## 2/ የስበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔ አባላት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቆሞስ አባ ሀ/ ኢየሱስ | | ለገሰ | አስተዳዳሪ | 46306684 |
| ኢ/ር | ይስሐቅ | ንጉሤ | ም/ሊቀመንበር፣ ኮንታክት | 97592932 |
| አቶ | ፍሬዘር | ተክሉ | ዋና ጸሐፊ | 98075044 |
| አቶ | ደረጀ | ሺታው | ም/ጸሐፊና ትራንስፖርት | 97726547 |
| አቶ | ዳዊት | አበበ | ንብረት ክፍል | 91774879 |
| አቶ | ግርማቸው | የወንድወሰን | ሕ/ግንኙነት፣መስተንግዶና ሺይዝጭ | 48621212 |
| » | እሙሽ | አሰፋ | ሂሳብ ሾምና ፎርስታንደር | 41667987 |
| ወ/ሮ | ያየሽ | ታደሰ | ገንዘብ ያዥ | 95527166 |
| አቶ | ዳንኤል | ታደሰ | ስብከተ/ወ/ክፍል | 98010817 |

## 3/ የሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዶ/ር | ተክሉ | አባተ | ሰብሳቢ | 93644054 |
| አቶ | ተዋሰን | ተሾመ | ም/ሰብሳቢ | 48137683 |
| አቶ | ዳንዔል | አበበ | ጸሓፊ | 45010673 |
| አቶ | አንዳርጋቸው | ስዩም | ገንዘብ፡ያዥና፡ሒሳብ | 94785936 |
| ዶ/ር | ዳዊት | አበበ | የአቅምግንባታ | 48354625 |
| ወ/ሮ | ሶስና | ግዛው | ፈንድሬይዚንግ ክፍል | 99479730 |
| አ/ቶ | ልዑል | አለማየሁ | ሕዝብ ግንኙነት | 91139611 |

በዚህ ዋና የሕንፃ አሠሪ ክፍል ሥራ የኢንጅነሮች፣የመሐንዲሶች፣ የፈንድሬይዚንግና የአማራጭ መንገዶች የተባሉ ንዑሳን ክፍሎች አሉት።

## 4/ የሰ/ት/ ቤት ከፍል

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አቶ | ደነቀ | አድማሱ | ሊቀ መንበር | 97713701 |
| ዶ/ር | ዳዊት | ሻውል | ም/ሊ መንበር | 48354625 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ወ/ሮ | ሜላት | ፍሥሐ | ጸሐፊ | 45070618 |
| አቶ | ጌታቸው | በቀለ | ሕፃናት ክፍል | 9844279 |
| አቶ | በጋሻው | ጎይሴ | ሥነ-ጽሑፍ ክፍል | 96984559 |
| ወ/ሮ | ሮዚና | ከንፈ | መዝሙር ክፍል | 45175662 |
| ወ/ሮ | ሰብለ | ተከሌ | ገንዘብ ያዥና ግንኙነት | 95064685 |

ሰንበት ት/ቤታችን ከዚህ ላየ ከጠቀሱት ንዑሳን ክፍሎች በተጨማሪ በሕፃናት ንዑስ ክፍሉ ሥር የወላጆች አቢይ ኮሚቴ እና ልዩ ልዩ ፮ የንዑስ ንዑስ ክፍሎች አሉት የሕፃናት ክፍሉም በሐፃናት እና ወላጆች ዙሪያ የሚያከናውነው ተገባር የሚያሸልም ነው።

## 5/ የስብከተ ወንጌል ክፍል

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አቶ | ዳንኤል | ታደሰ | ሰብሳቢ | |
| ዶ/ር | ተክሉ | አባተ | አባል | |
| ዲ/ን | አንዳርጋቸው | ስዩም | አባል | |
| አቶ | ጌታቸው | በቀለ | ጸሐፊ | |
| አቶ | ደነቀ | አድማሱ | አባል | |
| ወ/ሮ | አፎምያ | ሚካኤል | አባል | 90785219 |

## 6/ የዕቅድና ልማት ክፍል

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አቶ | ታደሰ | ገ/ሚካኤል | ሰብሳቢ | 45923703 |
| አቶ | ልዑል | መኰንን | ዋና ጸሐፊ | 97585703 |
| ዶ/ር | ሽጋው | አናጋው | ፕሮጀክት ማናጀርና ም/ጸሐፊ | 40672665 |
| አቶ | አበጀ | ወ/ብርሃን | አባል | |
| መ/ብሥራት አባ | | ሀ/ኢየሱስ ለገሰ | አባል | |

## 7/ የሕግና ሥነ-ሥርዓት ክፍል

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አቶ | ደምሰው | ተሰማ | ሰብሳቢ | 97602639 |
| » | ደረጀ | ሺታው | ጸሐፊ | 97726547 |
| » | እንግዳሼት | ታደሰ | አባል | 97100436 |
| » | ወርቁ | ታደሰ | አባል | 41380957 |
| » | ጌታቸው | በቀለ | አባል | |
| » | ተስፋዬ | በየነ | አባል | 48240997 |
| » | ንጉሤ | | አባል | |

# የ ፮ ወራት የሥራ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርት

## ፲ኛ/ በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር

- ባለፉት 6 ወራት 68 አባላትን መዝግቧል እየመዘገበም ይገኛል።
- በ2016 ቲል ስኩድ ለማግኘት የ790 አባላት ስም ዝርዝር ለፊልከስ ማን ተልኮ የነበረ ሲሆን ከነዚህም መካከል 578 ብቻ ተቀባይነት አግኝተው 212 በተለያየ ምክንያት ተቀባይነት አላገኙም ነበረ ሆኖም የጊዜ ገደቡ ካማለፉ በፊት አስቾኳይ ማጣራት ተደርጎ ከተመለሱት ውስጥ የ60 አባላት ስም ተስተካክሎ በድጋሜ ተልኳል። በደምሩ የ 638 አባላት ስም ተልኳል።
- ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ227 ብልጫ አሳይቷል።
- ለአባላት መታወቂያ ሰጥቷል እየሰጠም ይገኛል።
- ቤ/ክ በሀገረ ስብከት ጠቅላላ ሰበካ መ/ ጉባዔ ስብሰባ ላይ በአስተዳዳሪውና በምክትል ሊ/መንበሩ አማካኝነት ተሳትፋለች። በስበሰባው ላይ የ፳፲፮ ዓ/ም የሥራ ክንውን እና በውጭ ኦዲተር የተመረመረው የሂሳብ ሪፖርት እንዲቀርብ ተደርጓል።

- የ2015 የሥራክንውንና የሂሳብ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው በውቅቱ አቅርቧል። እንዲሁም የ2016 ዓመታዊ ዕቅድና በጀት በጣቅላላ መንፈሳዊ ጉባዔው እና በሊቀ ጳጳሱ አጸድቋል።
- የቤ/ክችን ዌብሳት ለማሻሻል ዐራት ባለሙያወችን በመመደብ የማሻሻልና የማሳደግ ሥራ ተሠርቷል ነው።
- የጎደሉ ወይም በሥራው ላይ ያልተገኙ የሰ/ት/ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሟሉለት ተደርጓል።
- በኢንተርናል ኦዲተር የተሠራው የ2015 ሂሳብ ሪፖርት በቤተ ክርስቲያናችን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከያዝነው ዓመት ዕቅድና በጀት እንዲሁም ከአለፈው ዓመት (2015) የሥራ ክንውን ዝርዝር ሪፖርት ጋር ማርች 10, 2016 ለብፁዕ አቡነ ኤልያስ የላከ ሲሆን በውጭ ወይም መንግሥታዊ የኦዲት መሥሪያቤት የተመረመረውን የሂሳብ ሪፖርትም በ01/09/2016 ኤልክትሮኒካሊ ለሀገረ ስብከቱ ተልኳል።
- ባለፈው ዓመት የሀገረ-ስብከቱ ጠቅላላ ሰበካ መ/ ጉባዔ በዓመታዊ ስብሰባው የወሰነውን አምስት በመቶ ወይም የሀገረ ስብከት 5%100 በውቅቱ ተልኳል።
- የሕግና ሥነ-ሥርዓት ክፍል ውስጠ ደንቡ በብፁዕ አባታችን አቡነ ኤልያስ እንዲጸድቅለት እና በአባላት ዙሪያ የሚከሠቱ ችግሮችን በማማከር የመፍታት ሥራ ጨምሮ እንዲሠራ ሦስት አዳድስ አባላት ተጭምረውለት በ፯ አባላት የተጣናከረ ሆኖ ሥራውን እንዲጀምር ተደርጓል።
- የቤተ ክርስቲያናችን የስብከተ ወንጌል ክፍል የውስጥ መመሪያ ድንብ በብፁዕ አባታችን አቡነ ኤልያስ ጸድቆ ክፍሉ እንዲመራበት ተደርጓል።

## የአውሮፓ ፲፱ኛው መንፈሳዊ ጉባዔ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ የሚካሄደው የአውሮፓ መንፈሳዊ ጉባዔ ከሰኔ 17 – 19 ቀን 2008 ዓ/ም (ጁን 24 – 26, 2016) በኦስሎ ቅዱስ ገብርኤልና አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦ/ተ/ ቤተ ክርስቲያን አዘጋጅነት እንዲካሄድ ቀድሞ በተወሰነው መሠረት የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔው ለአሠራር ያመቸው ዘንድ ይህ ጉባዔ እንደ ልዩ ፕሮጀክት ተቆጥሮ ወጪና ገቢን ጨምሮ በሁሉም መንገድ ራሱን በቻለ ግብረ ኃይል እንዲዘጋጅ አድርጓል።

- በዚህም መሠረት ከማቀድ ጀምሮ እስከፍጻሜው የሚያስተባብር ኮሚቴ በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔ፣ በኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴና በሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ የካቲት 23 ቀን 2008 ዓ/ም በማዮሽቱዋ ቤተ ክርስቲያን በተካሄደ ጥምር ስብሰባ ዐሥር የሥራ አሥፈጻሚ አባላትን ያየዘ የአውሮፓ መንፈሳዊ ጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴ እንዲቋቋም አድርጓል።
- ይህ ኮሚቴ ጉባዔውን በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ እንዲችል መመሪያ ደንብ አውጥቷል። በመመሪያም መሠረት ተንቀሣቅሶ የተቋቋመለትን አላማ በተሳካ ሁኔታ ፈጽሟል።
- ታላቁ ጉባዔ የወጣለት በጀት 130300 ነበር። ነገረ ግን ከ238 ምእመናን የተሰበሰበው የጉባዔው ጠቅላላ ገቢ 130782 ክሮነር የነበረ ሲሆን የወጣው የጉባዔው ጠቅላላ ውጪ 119063,14 ክሮነር ሆኖ ከወጪ ቀሪ 11718,86 ክሮነር ነው።
- በጉባዔው ላይ በተደረገ የፈንድሬዚግ ፕሮግራም የጉባኤው ሙሉ ወጪ ከመሸፈኑም በላይ ለቤተ ክርስቲያናችን የማይናቅ ገንዘብ ተሰብስቧል በሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ በኩል በተደረገ ጥረት 181000 (አንድ መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ) ክሮነር ተገኝቷል።
- ጉባዔው በኦስሎ ኖርዌ ለምትገኘው ቤ/ክናችን በርካታ መንፈሳዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያስገኘ ሲሆን ሁሉንም መዘርዘር ስለማይቻል ባለፈው ዓመት ከብዶን የከረመ ችግር በዘላቂነት የተፈታበት ጉባዔ ስለሆነ ሁል ጊዜ የሚታወስ ይሆናል።
- በዚህ ታላቅ ጉባዔ ላይ ፬ ታዳጊ ልጆች በበጹዕ አባታችን አቡነ ኤልያስ የዲቁና ማዕርግ ስለተሰጠልን ከዲያቆን ችግር አርፈናል።
- በሰመር የዕረፍት ጊዜ በቤተ-ክህነት ት/ቤት ደረጃ ዲያቆናትን የማሰልጠንና ተዳጊ ሕፃናትን ፊደልና የቃል ት/ትምህርት የማስተማር ሥራ ተሠርቶ ውጤት ተገኝቷል። ዲያቆናቱ ከዚሁ ተወልደው ያደጉ እንደመሆናቸው አማርኛ ማንበብ ስለሚከብዳቸው ከጁላይ 4,2016- ኦገስት 22,2016 ከሰኞ እስከ ዐርብ 12፡00 እስከ 15፡00 በቀን ለ3 ሠዓት በአካል በቤ/ክ ይካሄደ በነበረ እልክ አስጨራሽ ጥረት ዲያቆናቱ አመክንዮ፣ በእንተ ቅደሳት እመቦና የመሳሰሉትን ምንባባት አጥርተው ማንበብና መልእክታትንም በግፃዌው መሠረት ራሳቸው እያወጡ ለማንበበ እንዲችሉ ማድረግ ተችሏል።

- ከ4ቱ ዲያቆናት በተጨማሪ ለሌሎች 10 ወንዶችና ሴቶች ታዳጊ ሕፃናት የፊደልና የቃል ት/ት የተሰጠ ሲሆን አብዛኞቹ የፊደልን ጓዝና የቤተ-ክርስቲያናችንን የግእዝ ቁጥሮች አጣናቀው ፊደለ ሐዋርያን በግእዝ፣በውርድና በዓቢይ (ቁም) ንባብ ጨርሰው ገበታ ሐዋርያ የጀመሩበት ሁኔታ በውጭው ዓለም የማይቻል መስሎ የሚታየውን ባህላዊውን የቤተ/ክ (አብነት ትምህርት) ማስተማር እንደሚቻል ያረጋገጥንበት ነበር። ይህም ሥራ ዐርብ አርብ 17-19፡00 ሠዓት በአካል ቅዳሜ ጧት ጧት በስካይፕ እንዲቀጥል ተደርጓል።

## ንብረትን አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ

- በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ለተከናወኑ አበይት ክብረ በአላትና ሰንበት አገልግሎት የሚውሉ መገልገያ እቃዎች ተገዝተው ደረሰኞቹም ተወራርደው ሂሳብ ክፍል ገቢ ተደርገዋል።
- ከመቅደስ ውጪ የንብረት ቆጠራ ተካሂዷል።
- አዲስ ከምእመናን በስጦታ የገቡና በወቹ የተገዙ ንብረቶች በወቅቱ በንብረትነት ተመዝግበው በጥንቃቄ ተይዘዋል።

  ለምሳሌ፡- አራት አዳዲስ ስጋጃ ምንጣፎች በ 6500 ክሮነር የተገዙ ሲሆን 2900 ክሮነር ከቅድስት ቤተክርስቲያን ወጪ ሆኖ ቀሪው 3600 ክሮነር ከምእመናን በተገኘ ተሸፍኗል። የመንበር መጋረጃና ልብስ ወጪው በአባታችን በመላከ ብስራት አባ ሀብተ ኢየሱስ የተሸፈነ፣ አንድ ዘመናዊ ቪዲዮ ካሜራ በቅድስት ቤተ-ክርስቲያናችን ወጪ የተገዛ፣ ማክራፎን እስከነ ሚክሰሩ ይጠቀሳሉ።
- ጥገና ለሚያስፈልጋቸው ንብረቶች የጥገና አገልግሎት ተከናውኗል።

❖ ችግሮች

- በንብረትነት የተመዘገቡ ስድስት ትልልቅ ቴሌቪዥኖች ( አንዱን በሎተሪ የደረሰው ምእመን መልሶ ለቤተክርስቲያን ያስገባው) በቦታ ማነስ የተነሳ በአቀማመጥ አለመመቸት ለብልሽት የመጋለጥ ሁኔታ
- ዘመናዊ የድምጽ ማጉያ (ሚክሰርና ሳውንድ ሲስተም) በተሟላ ሁኔታ ተገዝቷል።

## የህዝብ ግንኙነትን በተመለከተ

- የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ባለፉት ፮ ወራት ውስጥ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የተለያዩ ተግባራቶችን ያከናወነ ሲሆን ከነዚህም መካከል፤
- ከ፮ ወር በፊት ቀርቦ በነበረው የቤተ ክርስቲያኗ ዓመታዊ ስብሰባ ጊዜ ከምእመናን በደረሰው ጥቆማ መሠረት የሃሳብ መስጫ ሣጥን አዘጋጅቷል፤
- በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አስቸኳይ የሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፣ እንዲሁም በቤ/ክችን ለሚከበሩ ለዓመትና የወር በዓላት ለምእመናንና በአካባቢያችን ለሚገኙት መሰል አብያተ ክርስቲያኖች በተቻለ ፍጥነት መልክቱን በSMS፣ በኢ-ሜልና በቫይበር አስተላልፏል፣
- ለ፴፬ኛው የአውሮፓ መ/ጉባኤ በአውሮፓ ለሚገኙ መሰል አብያተ ክርስቲያናት ከ፫ ወር በፊት የጥሪ ደብዳቤ ልኳል፣ እንዲሁም ወቅቱን ጠብቆ ተከፍቶ በነበረው የፌስ ቡክ ድህረ ገፅ ላይ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ማስታወቂያዎችን በመልቀቅ በዓለም ላይ ለሚገኙ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መልክቱን አስተላልፏል፤
- የቤተ ክርስቲያናችንን ድህረ ገፅ (website) ጥራቱን ማሳደግ፤ የድህረ ገፁ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን በቅርብ ጊዜ አዲሱ ድህረ ገጽ በሥራ ላይ ይውላል፤
- የቤተ ክርስቲያናችንን አባላት ቁጥር ማሳደግ እየተሠራበት ሲሆን በዚህ ፮ ወር ውስጥ ፰ አዳዲስ አባላትን እንዲመዘገቡ በማድረግ የበኩሉን አስዋጾ አድርጓል፤
- በሕዝብ ግንኙነቱ አስተባባሪነት ለቤተ ክርስቲያናችን የቅዳሴ ሥርዓት አገልግሎ የሚውል አንድ ላፕቶፕ ከምእመናን በስጦታ ለቤተ ክርስቲያኗ ተበርክቷል፤
- ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል አዲስ የቪዲዮ ካሜራ፤ ተገዝቶ ከአለፈው የአውሮፓ ጉባኤ ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል።

## ሂሳብን

ሂሳብን በተመለከተ የ 6ቱ ወራት ሂሳብ አጠር ብሎ አጠርና ጠቅለል ብሎ ሲቀርብ እንደሚከተለው ይሆናል።

| | ገቢ | ወጪ |
|---|---|---|
| January | 101 786 | 159446 |
| February | 123947 | 53161 |
| March | 53785 | 190504 |
| April | 215860 | 271079.56 |
| May | 56813 | 54558.54 |
| June | 360291.20 | 209583.23 |
| ጠቅላላ የገቢና ውጪ ድምር | 912 482,20 | 938 332,33 |
| ልዩነት | | -25 849 .55 |

## የንዋየ ቅዳሳት ሱቅ

| በንዋየ ቅድሳት ሱቅ ከሽያጭ በ፮ ወራት የተገኘ ገቢ 2016 | |
|---|---|
| ወር | መጠን |
| jan | 2086 |
| feb | 880 |
| mar | 545 |
| apr | 801 |
| may | 15 |
| jun | 5270 |
| ጠቅላላ ድምር | 9579 |

# ራሱን በቻለ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚንቀሳቀሱ ንዑሳን የአገልግሎት ክፍሎች የተከናወኑ የመንፈቅ ተግባራት።

## ፩ኛ/ የሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ

ሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ ከታሕሣሥ 22 ቀን 2008 ዓ/ም እስከ ሰኔ 23 ቀን 2008 ዓ/ም (ከጃኗሪ 1 ቀን 2016 እስከ ጁን 30 ቀን 2016) ድረስ በዕቅዱ መሠረት ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት፣ የገቢና ወጪ መጠን እንዲሁም በሥራዉ ሂደት ያጋጠሙት ተግዳሮቶች ቀጥለው በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

- ከሰበካ ጉባኤ ጋር ውይይታዊ ስብሰባ ማድረግና የተሻለ ሥራ በትብብር ማከናወን በዕቅዱ የነበረ ሲሆን የአውሮፓ ፲፱ኛው መንፈሳዊ ጉባዔን አስታኮ የጉባዔውን አዘጋጅ ኮሚቴ አብሮ ከማቋቋም ጀምሮ እስከ ፍጻሜው በረካታ ሥራዎችን አብሮ በመሥራቱ እቅዱ 100% ተከናውኗል። በአውሮፓ መንፈሳዊ ጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴ ውስጥ በሂሳብ ሹምነት፣ በገንዘብ ያዥነትና በጸሐፊነት ያገለገሉት የሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ አባላት ናቸው። እነዚህ አባላት ጉባኤው በማንኛውም እይታ ውጤታማ እንዲሆን ከሌሎች የጉባኤው አዘጋጅ ኮሚቴ አባላት ጋር የሚችሉትን ሁሉ አከናውነዋል።
- ከመንግሥት ቦታ የማግኘቱን ሂደት ተከታትሎ ምላሽ ማግኘትን በተመለከተ የአስሎ ማዘጋጃ ቤት ቤተ ክርስቲያን የምንገነባበት ቦታ ይሰጠን ዘንድ በብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ኤልያስ በተፈረመ ደብዳቤ ከአንድ ዓመት በፊት ጠይቋል። ከማዘጋጃ ቤቱ በተላከው የስልክ ጽሑፍ እንደተገለጸው ከሆነ ቀድሞ ተገኝተው የነበሩት ሁለት ባዶ ቦታዎች በከተማው አስተዳደር ለልማት ሥራ ስለሚፈልጉ ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት ባዶ ቦታ በከተማው እንደሌለ የተገለጸ።ውጤቱ የተጠበቀ ግን የማይፈለግ ቢሆንም እቅዱን ተግባራዊ ለማደረግ በተደረገው ተደጋጋሚ ክትትልና ጉትጎታ ሰኔ 21 ቀን 2016 ይህ መልስ ሊገኝ ችሏል።

➢ ኮሚቴው ይህን መልስ ከመስማቱ በፊት ሁለቱ ባዶ ቦታዎች በሚገኙበት በግሩሩድ ክፍለ ከተማና በአካባቢው የሚኖሩ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ብዛት እንዳላቸውና የማምለኪያ ቦታ እንደሚያስፈልጋቸው በመስተዳደሩ ውስጥም ሁለት ባዶ  ቦታዎች እንዳሉ የሚገልጽ ደብዳቤ ተጨማሪ ደብዳቤ ልኳል። የኦስሎ ማዘጋጃ ቤት ከሰጠው  መልስ በመነሳት ቦታ የማግኘቱ እድል እጅግ የጠበበ ቢሆንም ኮሚቴው ከግሩሩድ ክፍለ ከተማ መልስ በመጠበቅ ላይ ይገኛል።

➢ ክፍት ቦታዎችን ወይም ሕንፃዎችን ማፈላለግን በተመለከተ ለኦስሎ ማዘጋጃ ቤት የተጻፈውን ደብዳቤ ከመከታተል ጎን ለጎን ሌሎች አማራጮችም ሲታዩ ነበር። ባዶ ቦታዎችን ወይም ሕንፃዎችን ማፈላለጉ አሁንም እንደቀጠለ ነው።

➢ የክርስትና እምነት ተቋማት ስለ ቤተክርስቲያናችን እንዲያውቁ ማድረግን በተመለከተ የሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ ከኖርዌይ መንግስት ባዶ ቦታ ማግኘት እንደማይቻል አስቀድሞ ባደረገው የዳሰሳ ጥናት ተገንዝቦ ከኦስሎ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ጽ/ቤትና ከጳጳሱ ቢሮ ጋር ቅርብ ግንኙነት መፍጠርን ወሳኝ አማራጭ አድርጎ ይዟል። በመሆኑም ኮሚቴው ባለፈው ዓመት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን ያለችበትን ሁኔታ ለነዚህ አካላት በተለያዩ  ስብሰባዎች ላይ ገለጻ ማድረጉ ይታወሳል። ለምሳሌ ግንቦት 13 ቀን 2008 ዓ/ም (ሜይ 21 ቀን 2016) በተደረገው የጸድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የንግሥ በዓል ላይ እንዲገኙ የአውሮፓና የአፍሪካ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ገብረ እግዚአብሔርን ጨምሮ የኖሽክ አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ ባለ ሥልጣናት እንዲሁም የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎችን ጋብዟል ። በተለይ የኖሽክ አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ ባለ ሥልጣናት የቤተ ክርስቲያናችንን የአገልግሎት መጠን፣ የምእመናን ብዛትና የንግሥ ሥርዓታችንን በዐይናቸው አይተው ቤተ ክርስቲያናችን ምን አይነት ሕንፃ እንደሚያስፈልጋት በተጨባጭ እንዲረዱ ተደርጓል።

➢ እንሱም ብቻዋን በቋሚነት የምትገለገልበት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በማግኘት ሂደት ለመተባበር ዝግጁ እንደሆኑ በበዓሉ ላይ ባደረጉት ንግግር ጠቁመዋል።

➢ *ገቢ ማሰባሰብን በተመለከተ*  በመንፈቅ ዓመቱ የኢትዮጵያ ምሽት የተሰኘ የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ታቅዶ ነበር። ዳሩ ግን በ19ኛው የአውሮፓ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ቢሠራ የበለጠ ውጤት እንደሚገኝ ስለታመነ ከሰበካ አስተዳደሩ ጋር በመነጋገርና በመስማማት በዚሁ ጉባኤ ወቅት ከልዩ ልዩ ገቢ የማግኛ ዘዴዎች 181 000 (አንድ መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ) የሚሆን ክሮነር በጥሬ ገንዘብና በቃል ኪዳን መልክ ተገኝቷል።

➢ ከባንክ ብድር ማግኘት ይህን ጉዳይ በተመለከተ ባዶ ቦታ ወይም ሕንፃ ለሽያጭ ከወጣ ወዲያውኑ ለመጫረትና ለመግዛት የመነሻ ካፒታል እንደሚያስፈልግ ይታወቃል። በመሆኑም ዝግጁ ሆኖ ለመገኘት ኮሚቴው ምን ያህል ገንዘብ ከባንክ መበደር እንደሚችል የዳሰሳ ጥናት አካሂዷል። ለDnB ባንክ የብድር ጥያቄ አቅርበን የቤተ ክርስቲያናችንን ገቢና ወጪ ሁኔታ ከመረመሩ በኋላ የመበደር አቅማችን 6 000 000 (ስድስት ሚሊዮን) ክሮነር ብቻ እንደሆነ አሳውቆናል። ከዚህ በላይ ለመበደር ከተፈለገም የቤተ ክርስቲያናችንን ካፒታል ማሳደግ እንደሚያስፈልገን ታውቋል። ምናልባትም ሌሎች ባንኮች ከዚህ የተሻለ ብድር ይሰጡ ከሆነም ወደፊት ለማጥናት ታስቧል።

➢ ዘመናዊ የሂሳብ አሠራርን  ተከትሎ ይሠራል።

የሕንፃ አሠሪ የመንፈቀ ዓመቱ ገቢና ወጪ

| | January | Februar | March | April | May | June |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ገቢ ከምእመናን መዋጮ | 30494 | 31600 | 26450 | 10117 | 15217 | 16917 |
| ገቢ ከአውሮፓ ጉባዔ | - | - | - | - | - | 66750 |
| ወጪ - ለመጻሔት ህትመት | 12800 | 0 | 0 | 0 | 0 | - |
| ወጪ -ለሰበካ አ/ጉ/የተመለሰ | 4000 | - | - | - | - | - |
| ተቀማጭ ገንዘብ | 659090 | 690690 | 717140 | 727257 | 742474 | 826141 |

➢ በአውሮፓ መንፈሳዊ ጉባኤ ወቅት በተደረገው ሥራ 181 000 (አንድ መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ) ክሮነር በጥሬ ገንዘብና በቃል ኪዳን መልክ እንደተገኘ ተገልጿል። ከዚህ ውስጥ 60 000 (ስድሳ ሺህ) ክሮነር እስከ ሰኔ መጨረሻ ባንክ የገባ ሲሆን ቀሪው ገቢ በሐምሌ ወር ሪፖርት ይካተታል።

- በተጨማሪም ለጉባኤው በቤተ ክርስቲያናችን እቅድና ልማት ክፍል ከተገኘውና ከምእመናን ከተሰበሰበው ከወጪ ቀሪ 60 000 (ስድሳ ሺህ) የሚሆን ክሮነር እንደሚገኝም ይጠበቃል። ይህን ሁሉ ዝርዝር ያካተተ የሂሳብ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ኮሚቴው ያሳውቃል።
- ችግሮችና መፍትሔዎችን በተመለከተ:- የኮሚቴው ዋናው ተግዳሮት ለግንባታ የሚውል ባዶ ቦታ ወይም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል የሚሸጥ ሕንፃ አለመገኘቱ ነው።
- የኦስሎ ማዘጋጃ ቤት ቦታ እንዲሰጠን ጠይቀን እንደማይገኝ የሚገልጽ መልስ ለማግኘት 15 ወራት እንድንጠብቅ ሆኗል። ይህም ሆኖ ኮሚቴው በቀጣይነት ለሚከናወኑ ወሳኝ ድርጊቶች አዘጋጅ የሆኑ ሥራዎችን ሠርቷል።
- እንደ መፍትሔ ከኦስሎ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ጽ/ቤትና ከጳጳሱ ቢሮ ጋር ልዩ የሆነ ድርድርና ውይይት ለማድረግ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

## 2ኛ/ የስብከተ ወንጌል ክፍል።

- በሰኔ ወር 2016 ዓ/ም በተካሄደው አውሮፓ 19ኛው መ/ጉባኤ ላይ "በአውሮፓ መጪውን ትውልድ በቤተ ክርስቲያን ስለማስደግ" በሚል ርእስ የተዘጋጀ ዐውደ ጥናት እንዲቀርብ አድጓል።
- ለጉባኤው ይመጥናሉ፣የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በጠበቀ መልኩ ለምእመናን ተገቢውን ትምህርት ይሰጣሉ ብሎ የመረጣቸው መምህራን እና ዘማሪ እንዲመጡ ተደርጉአል።
- ለአውሮፓ ጉባኤ ሙሉ መርሐ ግብሩ በስብከተ ወንጌል ክፍል ወጥቶ ለአውሮፓ መ/ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ እና በጉባኤው ዕለትም ለምእመናን እንዲዳረስ ተደርጉአል። ጉባኤውም በመርሐ ግብሩ መሠረት በታቀደለት ሠዓት ተከናውኗል።
- በእየሳምንቱ የሚያገለግሉ መምህራን እና መርሐ ግብር መሪዎች በየተራ የሚያገለግሉበት ዕለት የሚያሳይ ሰንጠረዥ በማዘጋጀት ቀድመው እንዲያውቁት ከተደረገ በኋላ በዕቅዱ መሠረት ተከናውኗል።
- ባጠቃላይ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ መከናወን ካለባቸው የክፍሉ ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ አብዛኛው ተከናውኗል።ቀሪ እቅድ ክንውኖች በመጪዎቹ ስድስት ወራት ውስጥ የሚከናወኑ ይሆናሉ።

### ❖ ያጋጠሙ ችግሮች

- በስብከተ ወንጌል ክፍሉ ውስጥ የሚያገለግሉ አባላት በሌሎች ክፍሎች ውስጥ በኃላፊነት እያገለገሉ መገኘት የጊዜ መጣበብ እና የሥራ ጫና ፈጥሯል።
- በጊዜ መጣበብ ምክንያት መደበኛ ስብሰባዎችን በወቅቱ ለማካሄድ አልተቻለም።

## 3ኛ/ የዕቅድና ልማት

የዕቅድና ልማት ክፍል ባለፉት 6 ወራት ወስጥ የሚከተሉትን ተግባራት አከናዉኗል፡

- የክፍሉን አመታዊ እቅድ በማዘጋጀት በክፍሉ በያዝነው ዓመት መሠረት ያለባችውን ተግባራት በዝርዝር አስቀምጧል፣
- ቤተ-ክርስቲያንን በገንዘብ ለማገዝ ባወጣው ዕቅድ መሠረት አንድ ፕሮጀክት ሮፖዛል አዘጋጅቶ ሊከስቲሊንግ Likestiling ለተባለ የመንግሥት ድርጅት አቅርቦ የ 150 000 NOK እርዳታ አግኝቷል፡ ይህንን ገንዘብም በኦስሎ፣በሐመርና፣ በትሮምሶ ጉባኤዎችን ለማዘጋጀትና ምዕመናንን ያሳተፈ ትምህርት እና ውይይት በባለሙያዎች ለማካሄድ የመደበ ሲሆን፣ በኦስሎ ከአውሮፓ መ/ ጉባኤ ጋር፣ ተቀናጀቶ ተካሂዷል። በሐመርም ከሐምሌ ቅዱስ ኡራኤል ዓመታዊ በዓል ጋር አቀናጀቶ ላማካሄድና የመጨረሻውንና ሦስተኛውን የሊከስቲሊንግ /የቤተሰብና የእኩልነት ኮንፈረንስ የፊታችን አክቶበር 30፣ 2016 በትሮምሶ ለማድረግ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። ዝርዝር ሪፖርቱም በቀሪዎቹ ፯ ወራት የሚካተት ይሆናል።

- የክፍሉ የውስጥ መመሪያ ደንብ ተዘጋጅቶ በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔው ከታየ በኋላ በብፁዕ አባታችን አቡነ ኤልያስ መጽደቅ ስላለበት ለብፁዕነታቸው ተልኳል።
- በቤተ-ክርስቲያን በአባልነት ተመዝግበው ግን የቤተ-ክርስቲያን ተሳትፎአቸው ዝቅተኛ የሆነ ምዕመናንን ለመለየት እና ቀርቦ ለማነጋገር ሙከራ ተደርጓል በቀጣይም ይሠራል።

## 4ኛ/ የሰንበት ት /ቤት

- በመዝሙር ክፍል የታቀደው በአገልግሎት ዙሪያ የሚኖሩት ተግባራት አበረታች ቢሆኑም ክፍሉን የማጠናከር ሥራ በጣም አነስተኛ አነሥተኛ ሆኖ ተገኝቷል።
- የህፃናት ክፍል ሙሉ በሙሉ እቅዶቹን ማከናወኑ የሚያስመሰግን ነው።
- ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚጣበቅበትን በመወጣት፣ ግንኙነት ክፍል አባላትን በማብዛት ዙርያ ድክመት ያሳየ ሲሆን ሰ/ት/ቤቱ የተመሠረተበትን አንደኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በተለያዩ አርእስት የተዘጋጁ ጠቃሚ አርቶዶክሳዊ ትምህርቶችን በውስጧ የያዘች «ኀይለ አርያም» መፅሔትን ማሰራጨቱ ይበል የሚያሰኝ ሆኖ ተገኝቷል።
- በሰ/ት/ቤቱ ጽ/ቤት ይሠራል ተብሎ ከታቀደው አንፃር በአብዛያው እቅዶቹን ከ85% በላይ አከናውኗል።

❖ የነበሩ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

- የሰንበት ት/ቤቱን እስካሁን ከአቅም በታች እንዲሠራ ካደረጉት ምክንያቶች ዋንኛው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ያለመሟላታቸው የነበረ ሲሆን በቅርቡ ጉድለቱን የሚሟላት ሥራ ስለተከናወነ ችግሩ ተፈቷል።
- ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፡- የልጆችን ክፍል በበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በሚከናወኑ ሥራዎችና በሚደረጉ ጥረቶች የቤተሰብ ተሳትፎ ዋነኛው መሆኑ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል።

# ሌሎች ያጋጠሙ ታላላቅ ችግሮች

- ከላይ በሕንፃ አሠሪ ኮሚቴው ሥር እንደተገለጸው የራስ ቤተ-ክርስቲያን ለማግኘት በሚደረገው ጥረት በብድር፣ በባዶ ቦታና በሕንፃ ግዥ ዙሪያ የተጋረጡ ችግሮች።
- ምእመናን አሥራት የማያወጡ መሆኑና ወርኀዊ የአባልነት ክፍያቸውን በወቅቱ መክፈል አለመቻላቸው።
- የካህን እጥረት ትልቁ ችግር ነው። በመደበኛነት የሚያገለግሉት ካህን አንድ ብቻ ሲሆኑ ከአባላቱ ብዛትና የመንፈሳዊ አገልግሎቱና አሥተዳደራዊ ሥራው ስፋት አንፃር በቂ አይደሉም።
- የሰብካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባዔው ለስብሰባ በሚጠራበት ጊዜ አባላት ቢያንስ ግማሹ እንኳ መጥተው ወይም ተገኝተው የሚፈለግባቸውን ድጋፍና ገንቢ አሳብ መስጠት አለመቻላቸው።

# ማጠቃለያ

በተረፈው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በ1ኛው መለክቱ በምዕራፍ 4 ቁ 11 ላይ « *የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል»* እንዳለው በእናንተ አደራ የተሰጠውና የተመረጠው የአስሎ ቅዱስ ገብርኤል ወአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤ/ክ ሰ/መ/ አ/ ጉባዔ ከጠቅላላ ጉባዔውና ከሀገረ ስብከቱ የሚሰጠውን መመሪያ እየተቀበለ እግግዚአብሔር እደሰጠው ኀይልና ችሎታ የጻዳቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና የመልአኩ ቅ/ገብርኤል አማላጅነት በረዳው መጠን ለመሥራትና ለማገልገል ዝግጁ መሆኑን እየገለጽኩ ሪፖርቱን በዚሁ አጠናቅቃለሁ።

ሴፕቴምበር 18 ቀን 2016 /መስከረም 8 ቀን 2009) ዓ/ም

መ/ብ/ቆሞስ አባ ሀ/ ኢየሱስ ለገሰ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን።